# ግንቦት ሰባትን በተመለከተ የፃፍኩትም ሆነ የተናገርኩት የሚሰማኝን ሳይሆን የማውቀውን ነው።

ግንቦት ሰባትን በተመለከተ የፃፍኩትም ሆነ የተናገርኩት የሚሰማኝን ሳይሆን የማውቀውን ነው። ይህንን ተከትሎ አፍቃሪ ግንቦት ሰባቶችና ፣ ነፃነት የናፈቃቸው ንፁህ ወንድም እና እህቶች « የጎንዮሽ ትግል ምን ይሰራል ?» በማለት የተለያየ ጥያቄ፣ ምክር ፣ አስተያየት እና ሃሳብ ሰንዝረዋል ። እስከሚገባኝ ድረስ እኔ የጎንዮሽ ትግል እያደረግሁ አይመስለኝም። እኔ ከግንቦት ሰባት ጋር ፊት ለፊት ትግላ ላይ ነኝ ። ምክንያቴ ደሞ ግንቦት ሰባት በአማራ እርሾ እንጀራ ሊጋግር የሚጠራወዝ ምስኪን ሆኖ ስላገኘሁት ነው።

ባልዋሉበት ውለው ፣ ባልኖሩበት ኖረው ፣ የአማራን ትግል « እንደ መልዓክ እኛ የትም ነን እያሉ ፣ የትም ግን ሳይሆኑ » የወገኖቼን የደም ድል ለመንጠቅ ሲቧችሩ ሳይ ዝም አልልም ! የወልቃይት ጠገዴን ጥያቄ ደምሂትን ስለሚያስከፋ የማያነሱ ፣ አማራ ሲባል « እኛ ሃገራዊ ራዕይ የሰነቅን ነን ብለው ሲመልሱ » ባንፃሩ ግን ከሌሎች የብሄር ድርጅቶች ጋር ሲላላሱ እና ሲለሳለሱ እያየሁ ምን በጎን ያስኬደኛል ? ጥያቄዬ ፊት ለፊት ነው! ትግሌም ፊት ለፊት ነው ! ይህ የአንድ ጌኖክ የሺጥላ ድምፅ እና ሃሳብ መስሏችሁ ከሆነ አሁንም አደግመዋለሁ ስታችኋልም ተሳስታችኋልም !

የምታገላችሁ « ነፃነት የማያውቅ ነፃ አውጪ ስለሆናችሁ ብቻ አይደለም » የምታገላችሁ ፣ በነፃነት ፈፅሞ የማታምኑም እንደሆናችሁ ስለምረዳ ነው ። ይህንን የአማራ ወጣት ሊገነዘበው ይገባል ። አካሄዳቸውን እስካልመረመሩ ድረስ ፣ እንደ ወያኔ እታገላቸዋለሁ! በአማራ እርሾ የፖለቲካ እንጀራ መጋገር እስካላቆሙ ድረስ እታገላቸዋለሁ! እርዳታ የሚሹ የአማራ ታጋዮችን ፣ ግንቦት ሰባት ከአማራ ህዝብ በሰበሰበው ገንዘብ ጠርንፎ ከስሩ ለማንበርከክ « ከኛ ስር ካልሆናችሁ አንረዳችሁም እያሉ ነብሳቸውን ለጥይት የሰጡ ወንድሞቻችንን መቀለጃ ማድረግ እስካላቆሙ ድረስ ዝም አልላቸውም ፣ አልታገሳቸውም ! የኔ ትግል የጎንዮሽ አይደልም ! የኔ ትግል የፊት ለፊት ነው ! ወደድክም ጠላህም ተንኮልህን ለህዝብ አስረዳለሁ። ይህንን የማደርገው ደሞ የአማራ ወጣትን ከሞት ለመታደግ ብቻ ሳይሆን ፣ የአማራ ወጣት ታግሎ ሲሞት ድሉም ሆነ ተጋድሎው የራሱ የአማራው እንደሆነም ሳትፈልግ በግድ ተገደህ እንድትቀበልም ነው! እውነቱ ያ ነዋ!

ጌኖክ የሺጥላ